**Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto**
**ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ**
E-mail: torontofinote@gmail.com

## ለኢትዮጵያ ሕዝብ እየተደገሰ ያለው የጥፋት ድግስ
## በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ይከሽፋል፤ ሕዝብ አገሩንም ከጥፋት ያድናል!

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቃይና ፈተና አብቅቷል የተባለበት ግዜ ሳይሆን፤ በአዲስ መልክ የዘረኝነቱ፣ የአፈናው፣ የእጅ አዙር የውጭ አገዛዝ የቀጠለበት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎትና ጥያቄ ሳይሆን የጎረቤት፣ የኃያላንና የአረብ አገሮች ጥቅምና ፍላጎት የሚጠበቅበት ጊዜ ሆኖ እየተመቻቸ ነው፡፡ ለዚህም ደግሞ ታማኝ አገልጋይ ሎሌ አሰልጥነውና አዘጋጅተው በለውጥ ስም ያስቀመጡ መሆኑን በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ እያየን ነው፡፡ እኛ በዘር ፖለቲካ ስንታሽ ከላያችን የኃያላንና ቱጃር አረብ አገሮች ሎሌያቸውን በለውጥ መሪ ስም አስቀመጡብን፡፡ ተወደደም ተጠላም ሀቁ ይህ ነው፡፡ የዋሁማ እውነት መስሎት 'ከእግዚአበሔር የተላከ መሪ አገኘን' ብሎ ነበር፡፡ ከድጡ ወደ ማጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ግን ብዙ ጊዜ ወሰደብን፡፡

ያለፉትን 28 ዓመታት ወያኔን/ኀወሐትን አስቀምጠውብን ያንን ሁሉ ጥፋትና የሕዝብ እልቂት ሲያካሄድ፤ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሌት ተቀን፣ ክረምት ከበጋ ሲጮኹ ድፍን ዓለም ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት እንዲያውም ለ27 ዓመት በየዓመቱ ከ አንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የበጀት ድጋፍ ስታደርግ የቆየችው አሜሪካ 'መለስ የጸረ ሽብርተኛ አጋራችን ሰለሆነ እንደግፈዋለን' በማለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰቃይና እልቂት፣ ሰደትና መከራ ሆን ብለው በቸልታ ሲያዩና ሲያናንቁ ቆይተዋል፡፡ የአውሮፓም ኃያላን አገሮች አልፎ አልፎ መግለጫ ከማውጣት በቀር ፖሊሱን፣ ጦሩን ሲያሰለጥኑ፣ እርዳታና ብድር በገፍ በመስጠት በኢትዮጵያ ሕዝብ ቁስል ላይ ጨው ሲነሰንሱ መቆየታቸው አይዘነጋም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በክልል ተሸንሽኖ ሕዝብ ከሕዝብ ሲያለያዩና ሲያጋጩ፣ በአማራው ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የሕዝብ እልቂት (genocide) ሲፈጸም ምንም እንዳልተደረገ ወይም እንዳልሰሙ ሲያስመስሉ፣ የአኝዋክ ህዝብ ሲጨፈጨፍ እና እልቂት ሲፈጸም ከከንፈር መጠጣ በቀር አንዳች ነገር ሳይሉ፤ በሽብርተኛ ስም የኦጋዴን ህዝብ ላይ እልቂት ሲፈጸም በዝምታ አልፈው፣ በአገር ወስጥ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ከመኖሪያው ሲፈናቀልና ለከፋ አደጋ ሲጋለጥ ከዜና ሽፋን በቀር ምንም ሳያደርጉ ሲያልፉ ቆይተው፤ የዛሬ ሁለት ዓመት የተነሳው የሕዝብ አመጽ ስላሰጋቸው ግን ለዓመታት ሲያሰለጥኑና ሲያዘጋጁት በቆዩት ሹመኛ አማካይነት ትግሉን አስጠልፈው የሀሰት የለውጥ ነጋሪ ሲያስጎስሙና የዓለም የዜና ሽፋን ሲሰጡ፤ ያው እንደተለመደው **ለ28 ዓመት ሲጋልቡትና አገልጋያቸው ሆኖ የቆየው የኀወሐት በቅሎ ሲያረጅባቸው ያንን በ ኦዲፓ በቅሎ ኮሎኔል አብይ አህመድ ከመቀየር በቀር ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈይድ አዲስ ነገር አልመጣም፡፡** የለም፡፡

ዛሬም ያው አፋኝና ከፋፋይ ጨቋኝ ሕገ መንግሥት፣ ጸረ ዲሞክራሲ አገዛዝ፣ የዘር መከፋፈሉ ስርዓት በባሰ ሁኔታ እንዲቀጥል እያደረጉ ነው፡፡ በአይናችን እያየን በየቀኑ በገጠርና ከተማ ሰው ሲገደል፣ በገጀራ ሲታረድ፣ በእሳት ሲቃጠል፣ ከቤት ንብረቱ ሲፈናቀል፣ ሲታሰር፣ ሲሰደድ፣ የተደራጁ የወንበዴ ቡድኖች ኢላማ ሆኖ ሲሰቃይ፣ ታይተውና ተሰምተው የማያውቁ ወንጀሎች ሲፈጸሙ፣ የነገ አገር ተረካቢ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ሲገደሉ፣ ከፎቅ ሲጣሉ፣ በጩቤ ሲወጉ፣ ሲደበደቡ፣ ሴቶቹ ሲደፈሩ፣ ሲታገቱ እየሰማን እያየን አይደለምን? መጠኑ ያልታወቀ ገንዘብ ከ 18 ባንኮች ሲዘረፉ ዝም የሚል መንግሥት፣ በአንጻሩ የወያኔ የግድያ ሴራ በየቦታው ሲፈጸም ችላ እየተባለ፣ የኦሮሚያ ክልል በየቀኑ የሰው እልቂትና ጦርነት ቀጠና ሆኖ ዜና ሲሰማ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብዬው ቤተመንግስት መዝናኛ ሲያሰራ፣ አዲስ አበባ ከተማን ሲያጸዳ፣ ዛፍ ሲተክልና ወሃ ሲያጠጣ ከመታየት በቀር ወይንም የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያውቀውን ምስጢራዊ ስምምነት ለመፈጸም በየሀገሩ ከመዞር በቀር ስለ አንዱም ግድያ፣ እልቂት፣ ዝርፊያና መፈናቀል መግለጫ ሲሰጥ፣ ሲያስቆም አልታየም፡፡ ከዚያ ይልቅ በዓለም አቀፍ ሚዲያዎች በየአገሩ ሲሸለምና ሲሞካሽ ከመስማት ውጭ እንደ አንድ አገር መሪ ሲጠየቅ አለመስማታችን ምን ያህል ዓለም አቀፍ ሴራና ዱለታ እንደተሴረብን መረዳት ከባድ ነገር አይደለም፡፡ እነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌንና የነ ዶ/ር አምባቸውን አመራር ካጠፉ በኋላስ ምን እያደረጉ ነው?

በቅርቡ ደግሞ የኦሮሚያ ክልል እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ የሆነ ‘በልዩ ፖሊስ ሀይል’ ስም የጦር ሰራዊት ያሰለጠነው፣ በአሜሪካ፣ ጀርመን፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ እርዳታ እየሰለጠኑ ያሉት ስራዊቶች ለማንና ለምን ይሆን? ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን፡፡ አረቦችም በሚሊቴሪውና በደህነነት ተቋም ውስጥ እጃቸውን እያስገቡ መሆኑን እያየን፣ እየሰማን ነው፡፡መልሱ ግልጽና ቀላል ነው፡፡ ከጥቂት ወራቶች በኋላ ምርጫ ይካሄዳል ተብሏል፡፡ ይህ ምርጫ በህዘብ ትግል አሸናፊነት ቢጠናቀቅ ወይም ምርጫው ተጭበረብሮ ሕዝብ ቢያምጽ ጸጥ ለማሰኘት ነው፡፡ ይህን ምርጫ ያስቀመጡት በቅሎ በአሸናፊነት ተወጥቶ፤ አገሪቷን በውጭ አገራት ተጽዕኖ ሰር አስቀምጦ የፈለጉትን ለማድረግና የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብት ለመበዝበዝ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ በእርዳታና በብድር ስም የሚሰጠው ገንዘብ በአስር እና ሃያ እጥፍ ተመልሶ ይመዘበራል፡፡ አረቦችም ኢትዮጵያ እንዳትጠናከር፣ በራሷ ሰራዊትና መንግስት እንዳትቆም በመሻት ይህንን ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በጸጥታ ስም የሚደግፉትን ሎሌ ወታደራዊ አቅሙን አጎልብተው ያሻቸውን ያደርጋሉ፡፡














እነ ኦነግ/ኦዴፓ በመላ ሃገሪቱ ያፈለጋቸውን ወንጀል እያስፈጸሙ እንደልባቸው የጥፋት ቅስቀሳቸውን በምርጫ ስም ተያይዘውታል፡፡ አዲስ አበባ ያፈለጉትን ቦታ ባለጊዜ ነን በማለት ላሻቸው ባለጊዜዎች እያደሉ እየሰጡ ናቸው፡፡ የሩዋንዳ እልቂት አይነት ቅስቀሳቸውን በሚዲያ እያሰሙ እያሳዩ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ነገሩ ቀልድ ይምሰል እንጂ ይህን ሊንክ ብታዩት https://youtu.be/vDWLWpgvCg መልእከቱ ወዴት እያመራን መሆኑን ጠቋሚ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከመቼ ነው ጸጥታውና ሰላሙ ደፍርሶ የሚኖረው? እስከመቼ ነው ያልመረጠውና ያላስቀመጠው ጉልበተኛ በመንግሥት ስም ላዩ ላይ ተቀምጦ ሲረግጠውና ሲያፍነው የሚኖረው? እስከ መቼ ነው የተፈጥሮ ሀብቱን ለውጭ አገራት እያስበዘበዘ በድህነት የሚኖረው? እስከ መቼ ነው እምነቱና ባህሉ በሌሎች አገሮች መጤ ባህል ተውጦ ተገገር ትውልድ እያፈራ የሚቆየው? እስከ መቼ ነው ዲሞክራሲ ሳይኖር በአምባገነኖች እየተረገጠ የሚኖረው? ለዚህ መልስ የሕዝብ ፍላጎትና ጥያቄን በአግባቡ መመለስ እንጂ እናውቅልሃለን፣ እናሸጋግርሃለን በሚሉ ሃይሎች ስር መቼም ቢሆን መልስ አያገኝም፡፡ የነርሱ ዓላማና ተግባር የስልጣን ዘመናቸውን ማራዘም ሲሆን፤ ለሁሉም ጥያቄዎች መልስ የሚሆነው <u>**በኢትዮጵያዊ ሕዝብ ትግል ዘላቂ መፍትሔን መሻት በቻ ነው፡፡**</u>

ለዚህም ከዘርና ከጎሳ አመለካከት የጸዳ በኢትዮጵያዊነት መሰረት ላይ የጸና ትግል በአገር ቤትም በውጭም ሀገራት በማጠናከርና በማስተባበር ለሀገራችን ዘላቂና ቋሚ መፍትሄ መሻት ነው፡፡ በአሁኑም ወቅታዊ ሁኔታ ወያኔን በኦዲፓ መተካት ሳይሆን <u>**ብሄራዊ እርቅና ሰላም በመፍጠር፤ ሁሉንም ያካተተ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት መመስረት ብቻ ነው።**</u> ይህ ካለሆነ ግን የ 97ቱ ( 2005 እ.ኢ.አ) የተካሄደው የምርጫ ወጤት መደገሙ አይቀሬ ስለሆነ፤ ተቃዋሚ ኃይሎችና የፖለቲካ ድርጅቶች አቋማቸውን አስተካክለው ከምርጫው እራሳቸውን እንዲያገሉ እና ፈታኝና ወሳኝ የሆነ ሕዝባዊ ትግል በማካሄድ ያለውን አገዛዝ ማንበርከክ ይኖርባቸዋል፡፡ ትክክለኛ የትግል አካሄድ ይህ ብቻ ነው፡፡ ምርጫ ቦርድ፣ ታዛቢው፣ ሚዲያው፣ ፖሊሱ፣ ደህነነቱ፣ የፍትህ አካላት በገዢው ቁጥጥር ሰር ሆነው ወጤቱን ላለፉት 28 ዓመታት አይተነዋል፡፡ የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድ ባልተቻለበት አገር፣ ሰላምና መረጋጋት በሌለበት አገር ምርጫ ማካሄድ ፈጽሞ የማይሆን ነገር ነው፡፡ በዩነቨርስቲ ደረጃ እንኳን ትምህርት በሰላም ማካሄድ አልተቻለም እንኳንስ አገር አቀፍ ምርጫ ማካሄድ፡፡ ሕዝብ የሚያውቃቸው 'ተቃዋሚ መስለው የሚታዩ' የፖለቲካ ድርጅቶችና ሚዲያዎች ወቅቱ ሲደርስ ለኦዲፓ ሲያጎበድዱና ድጋፍ ሲሰጡና ሲለጠፉ እናያቸዋለን እና እውነተኛና እና አስመሳዩን መለየትም አንዱ ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡ የጨዋታው ቀልድ እንደተጀመረም እያየን ነው፡፡ ኮሎኔል አብይም ሆነ እነ ጃዋር የምርጫ ቀሰቀሳ ጀመረዋል እኮ ከምርጫ ቦርድ እውቅና፣ ፈቃድና ፐሮግራም ውጭ ተገበሩት፡፡ በፊትም ሕገወጥ ነበሩ፣ አሁንም ህገወጥ ናቸውም ወደፊትም ለመቀጠል እየሞከሩ ነውና ያንን መቃወም፣ ማስቆም ይኖርብናል፡፡

ምንም ተጽዕኖ ቢበዛ፣ የፈለገውን ያህል የገንዘብና የሚሊተሪ ድጋፍ ላለው ገዢ ቡደን ቢደረግለት፤ ወሳኙና አሸናፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ አስተማማኙም ይኸው ብቻ በመሆኑ ሁሉም የተቃዋሚ ኃይል ሊገነዘበውና ሊከተለው የሚገባውም ከሕዝብ ጎን መቆምን ነው፡፡ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመንና ፈረንሳይ የፈለገው አምባገነንና ጸረ ዲሞክራሲ ኃይል ቢኖርም ለእነሱ ታማኝና ታዛዥ እስከሆነ ድረስ አይናቸውን ጨፍነው ከመደገፍና ከመርዳት ወደኋላ አይሉም፡፡ ጥቅማቸውን እስካስጠበቀላቸው ደረስ የሕዝብ እልቂት፣ መፈናቀልና ሰደት ቢፈጠር ጉዳያቸውም አይደል፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታዎች ሁሉ የሚያሳዩትና የሚጠቁሙት ከፍተኛ ችግርና የጸጥታ መናጋት በቅርቡ መከሰቱ አይቀሬ መሆኑን ነው፡፡ የሕዝብ አመጽ ደግሞ አምባገነንን ለመጣል መነሳቱ አውን ነው፡፡ ይህን አመጽ ለመደምሰስ ነው ይህ ሁሉ የበላተረኛ አምባገነን ሰራዊት ኃያላን አገሮች ሰልጠናና ማስታጠቅ የያዙት፡፡ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ ህገወጥ መሳሪያ ሲገባ ይሰማል፡፡ ለዚህ ደግሞ ፍርሀትና ሽሽት ሳይሆን፤ በቆራጥነት በመስዋዕትነት አገርን ማዳን ይኖርብናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነቱ ሲቆምና ሲታገል የሚያሸነፈው ምንም ምድራዊ ኃይል እንደማይኖር ማሳየት ይጠበቅብናል፡፡ በአድዋ ወረራ ጊዜ አጼ ሚኒልክ ሕዝቡን አስተባብረው የጠላትን ጦር ድባቅ የመቱት ጠላትን አውቀውና ጠንቅቀው ተረድተው በጀግንነት በመዋጋታቸው ነው፡፡ ዛሬ ያንን ለማድረግ ምን ያዳግተናል? ለስልጣን ቋምጦ ከውጭ የገባው ሁሉ እግሬ አውጭኝ ብሎ እንደሚሸሽ በቅርቡ እናያለን፤ ጀግናው ኢትዮጵያዊ ግን የመጣውን ሁሉ ተጋፍጦ መታገሉ አይቀሬ ነው፡፡ ዋናው በሚገባ መደራጀትና ዝግጁ መሆን ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በቆራጥነትና ታግሎ አገሩንና ነጻነቱ ያስከበራል!

ሞት ለባንዳና ቅጥረኛ የጠላት አገልጋይ ሁሉ!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!